# <u>ጥለሽ ውጪ ቤቱን</u>

ሙሽሪት ፣ ምን ነካሽ ፣ አለቀ ወይ ፣ ፍቅሩ
ጫጉላ ቤት ፣ እያለሽ ፣ ሳያልቅ ግርግሩ
መልስ ሳትጠሪን ፣ ሞቅ ሳይል  ፣ ትዳሩ
ሀዘን ገባው ፣ ልብሽ ፣ ቀረ ወይ ፣ ባጭሩ ።

ካይነኬ ጋራ ፣ ፍቅር መጀመሩ
አይሆንም ብትባይ ፣ ሰው ፣ አለ ሀገሩ
ጆሮ ዳባ ፣ ብለሽ ፣ ወዳጆች ቢመክሩ
ቀድሞ ፣ አልሰማ ብለሽ ፣ አሁን ማማረሩ
በነጋ በጣባ ፣ ማዘን ማንጎርጎሩ
ማን ሊያስተዛዝንሽ ፣ ሊልሽ እሹሩሩ
ማፍረሱ ይሻላል ፣ አልሆነም ትዳሩ ።

ወዳጅ ፣ ዘመድ ሲመክር ፣ ብትሰሚ ኖሮ
ሰውን ባትንቂ ፣ አድርገሽ ደንቆሮ
ሀዘን ስታበዢ ፣ ለቅሶና እንጉርጉሮ
ከጎንሽ የሚቆም ፣ ሽንጦቹን ገትሮ
አይዞሽ ባይ ፣ ባልጠፋ ፣ ስታሰሚ እሮሮ ።

ለሰራሽው ስህተት ፣ ምክንያት መስጠቱን
ማማረሩን ትተሽ ፣ እሮሮ ማብዛቱን
የናቴ መቀነት ፣ ጠለፈኝ ማለቱን
ንትርኩን ትተሽ ፣ አስሩን ማውራቱን
ቢያቅርሽም እንኳን ፣ ተግተሽ እውነቱን
ዳግም ላትወሰልቺ ፣ ምለሽ ፣ አንድ ፊቱን
የታሰርሽበትን ፣ ሰብረሽ ሰንሰለቱን
ሳይመሽብሽ ቶሎ  ፣ ጥለሽ ውጪ ፣ ቤቱን ።

ታዛቢው … March, 10, 2010